# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የሽማግሌ ምትክ ምርጫ**

የሽምግልና አገልግሎት ዘመኑን በሚጨርሰው በወንድማችን ሲሳይ መሸሻ ምትክ ሽማግሌ ለመምረጥ በJanuary 5 (ዛሬ) ጥቆማ ይደረግና በJanuary 19 ምርጫ ይደረጋል። እንዲሁም የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ከሽማግሌች መካከል ይመረጣል። በዚሁ ቀንም የ2019 የቤተ ክርሲትያን ሪፖርት የሚቀርብ ይሆናል። ለዚህ ፕሮግራም እየጸለየን እንድንቆይ አናሳስባለን።

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

---

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ..."
(ዕብ. 13:20)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**January 5, 2020** | **ታህሳስ 26፤ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** ........................... | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| **አምልኮ**........................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............ | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| **ቃል** ................................ | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| **ማጠቃለያ** ..................... | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

### "መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።" (ኢሳ. 40:11)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### እግዚአብሔር እረኛዬ ነው።

መዝሙር 23 ዳዊት ከዘመራቸው ዝማሬዎች መካከል በጣም ታዎቂውና ተወዳጁ ነው። በዘመናት መካከል ይህ መዝሙር ብዙዎችን አበርትቷል፣ አጽናንቷል፣ እንዲሁም ተስፋ ሰጥቷል። በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ይህንን መዝሙር የጻፈው ንጉስ ዳዊት እራሱ እረኛ እንደ ነበረ ሁሉ የእግዚአብሔርንም መልካም እረኝነት በዚህ መዝሙር ውስጥ ውበት ባለው ቋንቋና ከሳች ምሳሌ ገልጾልናል። መዝሙሩ በእግዚአብሔር ላይ ያለ መታመንን በማጉላት መጋቦቱን፣ ምሪቱን፣ ጥበቃውን፣ አብሮነቱን፣ እና ዘላለማዊ እቅዱን ያሳያል።

የመዝሙሩ የመጀመሪያ አንጓ "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው" ይላል። በነዚህ ሶስት ቃላት እጅግ በጣም የታመቀ እውነታ ተቀምጧል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር የህዝቡ "እረኛ" ነው የሚለውን ሃሳብ እናገኛለን። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ እንደሆነ በስፋት ተዳሶ እንመለከታለን። ለምሳሌ በኢሳያስ 40:11 ላይ እግዚአብሔር "መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል" ተብሎ ተገልጿል። እዚህ ስፍራ የምናየው ምስል እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝቡ የሚራራ፣ ትጉ፣ አፍቃሪ እረኛ እንደሆነ ነው። መንጋውን በትኖ አይተዋቸውም፤ ይልቁንም በመልካም ስፍራ ያሰማራቸዋል። ሕጻናቱን ይሸከማል፣ የሚያጠቡትን አያስቸኩልም። በሕዝቅኤልም እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡን ቸል ያሉትን እረኞች በመውቀስ እርሱ ራሱ ለሕዝቡ እረኛ እንደሆነ ይናገራል። በተለይም ስለ እረኝነቱ ሲናገር "እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ አስመስጋቸውማለሁ...የጠፋውንም እፈልጋለሁ የባዘነውንም እመልሳለሁ የተሰበረውንም እጠግናለሁ የደከመውንም አጸናለሁ" ይላል (ሕዝ. 34፡15-16)። በአዲስ ኪዳንም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የበጎች "መልካም እረኛ" (ዮሐ. 10፡ 11) እንደሆነ ተገልጿል። ጌታችን ስለ በጎቹ ነፍሱን የሰጠ መልካም እረኛ ነው (ቁ. 11፣ 15)። ጌታ በፍቅር የሚመራ፣ እያንዳዱን በግ የሚያውቅ መልካም እረኛ ስለሆነ በጎቹ ድምጹን ያውቃሉ፣ ደግሞም ይከተሉታል (ቁ. 27)። የእብራውያን ጸሐፊም የጌታችንን ዘላለማዊ እረኝነት ሲገልጽ "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ" (ዕብ. 13:20) ይለዋል። የጌታችን እረኝነት ለዘላልም በደሙ ቃል ኪዳን የጸና ነው። ስለዚህም ከእጁ ማንም ሊነጥቀን አይችልም። ሐዋሪያው ጴጥሮስ ደግም የነፍሳችን "እረኛና ጠባቂ" እንዲሁም "የእረኞች አለቃ" (1ጴጥ. 2:25፣ 5:4) ይለዋል። እንዲሁም በመጨረሻ በጉ እረኞችን እንዲሚሆን ሐዋሪያው ዮሐንስ ሲጽፍልን "በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኞቻው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል" (ራዕ. 7:17) ብሏል። እግዚአብሔር ለዘላለምም የሕዝቡ እረኛ ነው።

ሁለተኛው በዚህ መዝሙር መግቢያ ላይ የምናገኘው ሃሳብ እግዚአብሔር በግል (ለእያንዳንዳቸን) እረኛ እንደሆነ ነው። ዳዊት የሚዘምረው የጅምላ መዝሙር ሳይሆን ከግል ልምምድ የወጣ፣ እግዚአብሔርን በማወቅ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን እረኝነት ነው። ስለዚህም "እግዚአብሔር እረኛዬ ነው" አለ። "እረኛዬ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን አጠቃላይ እረኝነት ብቻ የሚናገር ሳይሆን እግዚአብሔር የዳዊት እረኛ እንደሆነ ነው። ዳዊት የእግዚአብሔርን እረኝነት በሕይወቱ ተለማምዷል። እረኝነቱን በጦር ሰልፍ ያውቀዋል፣ እረኝነቱን በምድረ በዳ ያውቀዋል፣ እረኝነቱን በስደት ያውቀዋል፣ እረኝነቱን በብቸኝነት ያውቀዋል። ስለዚህም ዳዊት ይህንን መዝሙር የተቀኘው የአምላኩን እረኝነት በሕይወቱ ቀምሶ ነው። እኛስ ዛሬ እረኝነቱን በግል እየተለማመድን ነው ወይ? (ይቀጥላል)